የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ፤

ደንብና ስርዓት የስልጠና ሰነድ

አዘጋጅ ፋይናንስና ግዥ ዳየሬክቶሬት

ህዳር/2007 ዓ.ም.

የግዥ አፈፃፀም ስርዓት

መግቢያ

በግዥ ሥርዓት ውስጥ ግዥን በማስፈፀም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ለማስገኘት፣ በቁጠባ ለመሥራት የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እና ከፍተኛ የመንግሥት ገንዘብ የሚወጣበትን ግዥ ለማስፈፀም እንዲሁም የግዥ አፈጻጸምን ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና ደንብ ቁጥር 184/2002 ወጥቶ በተግባር ላይ ውሏል፡፡ በተጨማሪም የመንግሥት መ/ቤቶች የእቃና የአገልግሎት ግዥን እንዴት እንደሚያደራጁ እና እንደሚያከናውኑ አቅጣጫ እና ምክር መስጠት በአዋጅ የተሰጠው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በመሆኑ በተለያዩ ጊዜያት አፈጻጸሙን በመገምገምና አሠራሮችን በማስቀመጥ እየሠራ ይገኛል፡፡ በተለይ ከ2004 የበጀት ዘመን ጀምሮ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በወል ወይም በጋራ የሚፈለጉ እቃዎችን እና አገልግሎቶችን ግዥዎች በአንድ ማዕከላዊ ተቋም አማንነት አጠቃሎ መግዛት አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት የወጭ መገልገያ እቃዎች ግዥ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ማስወገድ አገልግሎት ጽ/ቤት በኩል እንዲከናወን እየተደረገ ይገኛል፡፡

2. የግዥ መመሪያን መሠረት በማድረግ የሚከናወኑ ግዥዎች

ሀ. የግንባታ ሥራ ግዥ

ለ. የዕቃና የአገልግሎት ግዥ

ሐ. የምክርና የአገልግሎት ግዥ

መ. ሌሎች የአገልግሎት ግዥዎች ይከናወናሉ፡፡

3. የግዥ መርሆዎች

1.ማናቸውም ግዥን ለማስፈጸም የተሰጠ ስልጣን እንዲሁም የግዥ አፈጻጸም የሚከተሉትን አላማዎች ግብ ማድረስ ይኖርበታል፣

1.1 በግዥ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም ማስገኘት ይህም ማለት ቁጠባን ውጤታማነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል በእየንዳንዱ ግዥ ውሣኔ መስጠትን ብቻ ሳይሆን የግዥ ዕቅድ የመኖርን አስፈላጊነት ይጨምራል፡

1.2 በአዋጁ በተፈቀደው ልዩ ተወዳዳሪ በዜግነት ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች አድልዎ ሊደረግበት አይችልም፣

1.3 ማናቸውም የግዥ ውሣኔ የሚሰጥባቸው መስፈርትና በእያንዳንዱ ግዥ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልጽ ማድረግ አለባቸው፣

1.4 ውሣኔዎችና የተወሰዱ እርምጃዎች የሚያስከትሉት ተጠያቂነት ጥብቅ እንዲሆን መደረግ አለበት፣

2. በአዋጁ የተፈቀደው ልዩ አስተያየት እንደተጠበቀ ሆኖ የእቃዎቹ ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ጥራትና ዋጋ ተመሳሳይ በሚሆንበት ጊዜ ለሀገር ውስጥ ኩባኒያዎች ቅድሚያ ይሰጣል፡

3. የግዥው ወጪ የሚሸፈነው በውጭ ብድር ወይም ዕርዳታ በሚሆንበት ጊዜ የግዥው አፈጻጸም በብድሩ በእርዳታው ስምምነት መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል።

እነዚህ መርሆዎች መሠረት በማድረግ ከላይ የተገለጹትን አራት የአገልግሎት ግዥዎች ለመፈፀም ግዥው፡-

ሀ. የግዥ ህግን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፣

ለ. ግልጽነትና ተጠያቂነትን ያለበት አሰራር መሆን አለበት

ሐ. ትርፍን ወይመ ጥቅምን ማእከል ያደረገ መሆን ይገባዋል፣

በተጨማሪም ወጪ ቆጣቢና በጀትን ያማከለ ግዥ ለመፈጽም እንዲቻል የቁጥቁጥ ግዥዎችን ለማስቀረት ግዥን በጥቅል መፈጸም ጠቃሚና ተመራጭ ነው። በዚህ መሠረት ግዥዎችን ለመፈጸም፣-

1. የግዥ ፍላጎትን ማሰባሰብ
2. የግዥ ዕቅድን ማዘጋጀት
3. የበጀት አቅምን ማረጋገጥ
4. የግዥ ዘዴዎችን መምረጥ

4. የግዥ ዘዴዎችና አፈጻጸማቸው

የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች ስድስት ሲሆኑ

1/ ግልጽ ጨረታ

2/ ውስን ጨረታ

3/ የሁለት ደረጃ ጨረታ

4/ በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ

5/ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ

6/ ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም

4.1 ግልፅ ጨረታ

ሁኔታዎች ካላስገደዱ በስተቀር ማንኛውም የመንግሥት ግዥ በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም አለበት ብዛት ያላቸውን እቅራቢዎች እንዲሳተፉ ለማድረግ የግልጽ ጨረታ አፈጻጸም ጠቃሚ ነው

ግልጽ ጨረታ ሁሉንም ህጋዊ ተጫራቾች እኩል እድል ሊሰጥ ይችላል፡፡ ከበርካታ ተሳታፊዎች የውድድር ተሳትፎ ከፍተተኛ የዕቃ የአገልግሎት ጥራትና ያልተጋነነ ወይም ተመጣጣኝ ዋጋ ያስገኛል፡፡ የመንግሥት ግዥ መሠረታዊ መርሆዎችን በተሻለ ተግባራዊ ለማደረግ ያስችላል፡፡ ለህዝብ እይታ ግልጽና ለቁጥጥር ያመቻል አቅራቢዎች የውድድር ተሳታፊ ሊሆኑ ይስችላል፡፡

4.2 ውስን ጨረታ

የውስን ጨረታ አፈጻጸም ሥርዓት ከግልጽ ስርዓት አፈጻጸም ጨረታ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን

ግዥውን በውስን ጨረታ ለመፈፀም ቢያንስ ለሁለት ጊዜ ወጥቶ ምንም ተጫራች ያልቀረበ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

አገልግሎቱ ወይም ግዥው ከተወሰኑ አቀራቢዎች የሚገኝ ከሆነ፣

ግዥው አስቸኳይነት ያለው ወይም በአፋጣኝ አለመቅረቡ የሚያስከትለው ችግር ከታመነበት፣

ውስን ጨረታ የሚካሄደው ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት አቀራብዎች መካከል በፐሮፎርማንሳቸው ጥሩ የሆኑትን ከ5 በላይ የሆኑ ድርጅቶችን በመምረጥ ይሆናል፣

ግዥ መጠኑ ለግንባታ በብር 2,000,000.00 ለእቃ ግዥ ከብር 500,000.00 ለምክር አገልግሎት ከብር 300,000.00 ለሌሎች አገለግሎቶች ከብር 400,000.00 ግዥው ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ ከሆነ እንዲሁም አስቸኳይ ከሆነ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን በላይ ቢሆንም የግዥ ኤጀንሲን ፈቃድ በመጠየቅ ሊከናወን ይችላል፡፡

4.3 የሁለት ደረጃ ጨረታ

ግዥው በባህሪይው ውስብስብ በመሆን ግዥ ፈጻሚው አካል የፍላጎት መግለጫ ወይም ቢጋር በማዘጋጀት አቅም ሳይኖረው ሲቀር የምርምር የሙከራ የጥናትና የልማት ሥራዎችን ለማከናወን በሚያስችል ውል ለመፈጸም ሲፈልግ

የእቃዎቹ ባህሪይ በፈጣን ቴክኖሎጂ ለውጦች ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣

የአፈጻጸም ደረጃው ሁለት ሲሆን ቴክኒካዊ እና ቴክኒካዊና ፋይናንስ ናቸው፣

4.4 በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ፣

ግዥው ሙሉ በሙሉ ወይም ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ የምክር አገልግሎቱ 50 በመቶውን እና በላይ ሲሆን የተዘጋጀው የፍላጎት መግለጫ ወይም ቢጋር እናሟላለን የሚሉ በውድድሩ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው አማካሪዎች ሐሳባቸውን እንዲገለጹ በማድረግ፣

በዚህ የግዥ ዘዴ ለመወዳደር የሚችሉ ከ3 እስከ 7 ተወዳዳሪዎች መምረጥ ይቻላል፣

4.5 በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ

እስከተቻለ ድረስ ከሶስት ካላነሱ አቅራቢዎች ኘሮፎርማ በመሰብሰብ የሚፈጸም ግዥ ነው፣

በዕቅድ ላልተያዙና ወዲያውኑ በሥራ ላይ ለመዋል የሚያስፈልጉ ለገበያ የተዘጋጁ ወይም የታወቀ ገበያና ዝቅተኛ መጠን ያላቸው ግዥዎች መፈጸም ሲያስፈልግ ነው፣

በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡ ይህን እድል ማግኘት ይጠበቅባቸዋል፣

ግዥዎችን ሆን ብሎ በመከፋፈል በቁጥቁጥ በዚህ ግዥ ዘዴ መፈጸም ነው፣

ውድድረን ለማረጋገጥ ቢያንስ የሶስት ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያ ኘሮፎርማ ያስፈልጋል፣

ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚላከው መጠየቂያ የሚፈለገውን ግዥ በትክክል የሚገልጽና ዋጋው የሚጸናበትን ጊዜ የሚያመለክት መሆን አለበት፣

ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያውን ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፣

በዋጋ ማቅረቢያው የሚገዛው ግዥ መጠን፣

ለግንባታ ስራ ግዥ እስከ ብር 250,000.00

ለዕቃ ግዥ እስከ ብር 100,000.00

ለምክር አገልግሎት እስከ ብር 600000.00

ለሌሎች አገልግሎት እስከ ብር 75,000.00

4.6 ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ

ተመራጭነቱ ዝቅተኛ የሆነ የግዥ ዘዴ ነው

ያለ ጨረታ ወይም ያለውድድር ከአንድ አቅራቢ ግዥ የሚፈፀም የግዥ ዘዴ ነው፣

ይህ የግዥ ዘዴ አገልግሎት ላይ የሚውልባቸው ሁኔታዎች፣

አንድ የተለየ አቅራቢ ብቻ የሚገኝ ሲሆን ነው፣

ግዥው በጣም አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሳ ካልተፈጸመ በመ/ቤቱ ሥራ አፈጻጸም ላይ ከባድ ችግር የሚፈጥርና ጉዳት የሚያስከትል ሲሆን፣

ቀደም ሲል በተካሄደው የጨረታ ውድድር አሸናፊ ከነበረ ተጫራች ላይ የቀድሞው ግዥ ውል ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ወይም ውሉ ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ በሚቀጥሉት 6 ወራት ውስጥ ተመሳሳይ እቃ ወይም አገልግሎት በተመሳሳይ ዋጋ ተጨማሪ አድርጎ መግዛት ሲፈልግ በገደብ የዋጋውን 25በመቶ ሲሆን፣

ከመጀመሪያው አቅራቢ ለተገጣጣሚዎች ተጨማሪ መለዋወጫዎች ለመግዛት ሲፈልግ ከሌላ አቅራቢ ቢገዛ መሳሪያው ወይም አገልግሎቱ መ/ቤቱ ከሚጠቀምበት ጋር የማይጣጣም ሆኖ በመገኘቱ ከመጀመሪያው አቀራቢ ግዥ ለመፈጸም ሲፈለግ፣

በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ነገር ግን ከመጀመሪያው ውል መነጠል የማይቻል ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች አስፈላጊ ሲሆን በገደብ የዋጋውን 30 በመቶ፣

5. የድርድር አፈጻጸም

ድርድር ማለት በገዥና በአቅራቢው አካል መካከል ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚደረግ ውይይት ሲሆን ይህም

- የምርት እጥረትና ለውጥ ሲኖር
- በጨረ|ታ ሰነዱ ላይ ባልተጠቀሱ የውል አፈጻጸም ጉዳዮች ላይ
- በዚህ አይነት የግዥ ዘዴ የሚፈጸሙ ግዥዎች ላይ በማናቸውም ዋጋ ጋር ግንኙነት በሌላቸው ጉዳዮች ላይ
- አቅራቢው እቃውን ለማምረት ወይም ገዝቶ ለማቅረብ ረዥም ጊዜ የሚወስድበት ሲሆን
- ያልተሟላ የፍላጎት መግለጫ ሲኖር፣
- ግዥው ከአንድ አቅራቢ በሚገዛ የግዥ ዘዴ ከሆነ በሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራት፣ብዛት፣ የማቅረቢያ ጊዜና ዋጋን ጨምሮ ከአቅራቢው ጋር በግልጽ በመደራደር የሚፈፀም ይሆናል፣

6. የድርድር ዓላማ

የድርድር አላማ በገዥው እና በአቅራቡው መካከል በግዥው መስፈርትና ሁኔታዎች ላይ ስምምነት ለመድረስ ነው

7. የድርድር አስፈላጊነት

- የተፈለገውን ዕቃ በአስፈላጊ ጥራትና ብዛት ባለው መልኩ ለማርካት
- ፍትሃዊና ተመጣጣኝ ዋጋ ለማግኘት
- አቅራቢው ውሉን በተፈለገው ጊዜ እንዲፈጽም፣

8. የድርድር ሂደቶች

8.1 የዝግጅት ሂደት

- ስለሚገዛው ቴክኒካል እውቀት
- የአቅራቢውን የመከራከር ጥንካሬ ማወቅ
- የግዥውን የመከራከር ጥንካሬ ማወቅ

8.2 ዓላማን የመለየት ሂደት

ተደራዳሪዎቹ የሚደራደሩባቸውን አብይ ነጥቦች ከዝግጅት ሂደቱ በመነሳት ባገኙት መረጃ አላማቸው /ሀሳባቸው/ ተለይቶ የሚቀመጥበት ደረጃ ነው

8.3 ፊት ለፊት ተገኝቶ መወያየት፣

እውነታን መፈለግ፡- የአቅራቢውን ጥንካሬ እና ድክመት ለማወቅ እንዲረዳው ገዥው አካል የአቅራቢውን ሰነድ በሚገባ በሚመረምርበት እና የሚፈትሽበትን ሂደት ነው፡፡

ማጣራት፡- እውነታን በመፈለግ ረገድ ላይ ዩተገኙ ነጥቦችን ከግምት በማስገባት የዋጋ ግምት ማስተካከያ ለማድረግ በድጋሚ ወደ ድርድሩ የሚመለሱበት ሂደት ነው፡፡

ልዩነቶችን ማጥበብ፡- ሁለቱ አካላት በመሃከላቸው የነበረውን ልዩነት ለማጥበብ እንዲረዳቸው ጉዳያቸውን በመዘርዘርና አንዱ አንዱን ለማሳመን የሚጠሩበት ሂደት ሲሆን ተደራዳሪዎቹ ያላቸውን መረጃዎች አማራጮችና መፍትሄዎች ለጋራ ጥቅም ሲሉ የሚያቀርቡበት የመጨረሻው ደረጃ ነው፡፡

9. አገልግሎት ፈላጊ ባለጀት መ/ቤቶችና ሌሎችም የግዥ አገልግሎት ለማግኘት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

በጋራ የሚፈለጉ እቃዎችን አገልግሎቶችን ዓመታዊ የፍላጐት መረጃን በዓይነትና በመጠን በመለየት ለግዥ ከተፈቀደላቸው በጀት ጋር በተገቢው ጊዜ ማሳወቅ፣

- በጨረታ ዝግጅትና ግምገማ ወቅት አገልግሎቱ የሙያ ድጋፍ ሲጠይቅ አስፈላጊውን ሙያዊ እገዛ ማድረግ፣
- በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በተገቢው ጊዜ መረከብ፣
- ከአገልግሎቱ በሚሰጠው የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት ከአሸናፊ ተጫራቾች ላይ ግዥ መፈጸም፣
- በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ርክክብ ከተፈጸመ በኋላ ክፍያ መፈጸም፣
- የተጠያቂነቱን መረጃና ማብራሪያ በተጠየቁበት ጊዜ ማቅረብ፡፡

<u>የግዥ ዘዴዎች (Procurement methods</u>

1. ግልጽ ጨረታ
2. ውስን ጨረታ
3. የሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ
4. በማወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ
5. በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ
6. ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ
   - የመንግስ ግዥ አጠቃላይ ገጽታ አላማና መርሆዎች

- ዓላማና መርሆዎች
- ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛው ጥቅም ማስገኘቱን Value for money
  1. ትክክለኛ ጥራት (Right Quantity
  2. " መጠን (Right Quantity
  3. " ዋጋ (Right Price
  4. " ጊዜ (Right Time
  5. " ቦታ (Right Source

1. ቅልጥፍናና ብቃት (Efficiency Effecfiuness
2. ቁጠባ Economic
3. ከአድሎ ነፃ የሆነ አሰራር መፍጠር Non discrimination
4. ግልጽነት (Transparency)
5. ለህዝብ ተጠያቂነት (Accountability)
6. ልዩ አስተያየት ማድረግ(Domestic preference)15%

- ለሀገር ውስጥ ምርቶች የ15% ልዩ አስተያየት ማድረግ፣
  - ስፔስፊኬሽን ማሟላት
  - ከምርቱ ዋጋ ቢያንስ 20% ኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ መሆን በተለይ ለመድሐኒቶች 25%፣ ለግንባታ ዘርፍ ስራ 7.5 % ልዩ አስተያየት ማድረግ ያስፈልጋል።
  - የውጭ ኩባንያም ከሆነ ከኩባንያው ሠራተኞች መካከል ቢያንስ 50%ኢትዮጵያን ሠራተኞች፣ የኩባንያው የዳይሬክቶሬት ቦርድ አባላት መካከል አብዛኛው ኢትዮጵያ ሲሆኑ እና ዋናው መ/ቤት ኢትዮጵያ ከሆነ የአክስዮን /የካፒታል/ ድርሻው አብዛኛው በኢትዮጵያን ከተያዘ ነው፣
  - ማንኛውም ግዥ በሚፈፀምበት ጊዜ በሶስት ነገሮች ላይ ተመርኩዞ መሆን አለበት፣

    1/ በመንግሥት ግዥ አዋጅ 699/2001

    2/ በመንግሥት ግዥ መመሪያ 184/2002

    3/ በመንግሥት ግዥ ማንዋል

  - የመንግሥት ግዥ ሕግ ዋና ዋና ይዘቶች፣
    - የመንግሥት ግዥ ኤጀንሲን ያቋቁማል
    - የግዥ ፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ኃላፊነት ይወስናል፣
    - መሠረታዊ የግዥ ድንጋጌዎችን ይገልፃል
    - የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎችን ይገልፃል
    - የግዥ ዘዴ አማራጭን ይወስናል፣
  - የግዥ ፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው
    - በተገቢው የሰው ኃይል የተደራጀ የግዥ የሥራ ክፍል ማቋቋም
    - የጨረታ ኮሚቴ የማቋቋምና አባላቱን የመሰየም
    - የሚገዙ እቃዎች /አገልግሎቶች ፋይዳ ከወጣበት ወጪ ጋር የሚመጣጠን መሆኑን/ value for money/ ማረጋገጥ

- የግዥ ውል ከመፈፀሙ በፊት ግዥ ለመፈፀም የሚያስችል በቂ በጀት መኖሩን ማረጋገጥ፣
  - የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣት
  - ከጨረታ ኮሚቴ የሚቀርብለትን ማናቸውንም ሃሳብ መርምሮ ውሣኔ መስጠት
  - የጨረታ አሸናፊዎችን መለየትና በዥ ጋር ግንኙነት ካላቸው ተቋማት ጋር የስራ ቅንጅት መፍጠር
  - የግዥ ጥናቶችን ማዘጋጀት
  - መደበኛ የጨረታ ሠነዶች/ Standard bidding document/ ማዘጋጀት
- የዚህ ሰነድ /Standard bidding document/ ዓላማው /ጥቅሙ/

  1/ የጨረታ ሰነዱን ዝግጅት ፈጣንና ቀልጣፋ ያደርገዋ

  2/ የጨረታ ሰነዱን ለማፅደቅ ይወሰድ የነበረውን ረጅም ጊዜ ያሳጥራል፣

  3/ተጫራቾች የግዥ ፈጻሚውን ፍላጐት በቀላሉ በመረዳት የመጫረቻ ሰነድ /offer ማዘጋጀት

  4/ለመንግሥት ግዥ አፈጻጸም ተስማሚ የውል ሁኔታዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ፣

  5/ ለመንግሥት ግዥ አፈጻጸም ተስማሚ የውል ሁኔታዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ

  6/ ደረጃውን የጠበቀና እንደ ግዥው ዓይነት እገልግሎት የሚሰጥ ወጥ ሰነድ መጠቀም ያስችላል፣

  <u>በግዥ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች</u>

1/ በየሥራ ክፍሎቹ የግዥ ፍላጐት በትክክል በጥናት ላይ ተመርኩኩዞ ያለመቅረብና በእቅድ ያልተያዙ ግዥዎችን ማቅረብ፣

2/ የግዥ አዋጁን ደንቡንና ማንዋሎችን በትክክል ተረድቶ ያለመተግበር፣

3/ የግልጽ ጨረታ ውስብስብነትና ዋጋ የሚጠይቅ መሆኑ፣

4/ የሚፈለጉ ግዥዎች በሚፈለገው መጠን፣ ጊዜ፣ አይነትና ጥራት አለመገኘትጀ፣